# ባንክ ለሚሰጠው አገልግሎት ስለሚከፈለው ክፍያ
# አዲስ የማሻሻያ ደንብ

*መመሪያ፦* ባንኮቹ ለሚሰጡት አገልግሎቶች ለመቀበል የሚጠይቁት ክፍያ ምን ያህል እንደሆን ማወቅ። ባንኮች ወይም ሎሎች ክፍሎች ለእያንዳንዱ ዓይነት አገልግሎት በሚያወጧቸው የዋጋ ተመንና አማራጭ በሆኑ ክፍሎች በሚወጡት የዋጋ ተመኖች መካከል ለማነጻጸር የወጣው አዲስ ደንብ

*የማሻሻያ ክፍያ ለውጡ (ሪፎርማው) እንዴት ሊረዳህ/ሽ ይችላል?*

ለባንክ አገልግሎት ክፍያው የማሻሻያ ለውጡ ከ1.7.2008 ጀምሮ በባንክ ለሚጠቀሙ ደንበኞች ባንኮቹ የሚያወጡትን የዋጋ ተመን በተመለከተ ተገቢ የሆኑትን መረጃዎች መስጠት ይጀምራል፤ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት በማነጻጸር በየትኛው ባንክ የባንክ ሒሳብ መክፈት እንደሚገባችሁ ወስኑና ምረጡ።

በአገልግሎትና ክፍያ ማሻሳያ ደንብ አማካኝነት የባንክ ደንበኞች እንዴት መንቀሳቀስና መወሰን እንዳለባቸው መወሰን ይችላሉ። በዚህ ዓይነት ሁኔታም ደንበኞቹ ለምሳሌ የባንክ ሒሳባቸው ካለበት ባንክ የበለጡ ጥሩ ጠቀሜታዎችን ከባንኩ መጠየቅ የሚያስችላቸውን፣ ወይም አሁን ካሉበት ባንክ ይልቅ የበለጠ ጥቅም ሊያገኙ ወደ ሚችሉበት ባንክ በመዛወር የባንክ ሒሳብ መክፈት ያስችላቸዋል።

ይህ የክፍያ ማሻሻያ ደንብ የባንክ ደንበኞቹ ወደ የበለጠ ብልህ የሆነ የባንክ አገልግሎቶች ተጠቃሚነት ይመራራቸዋል። ብልህ የሆነ ገበያተኝነት የባንክ አገልግሎቶችን ሁኔታና ሌሎች ሁኔታዎችንም በተመለከተ፤ በመካከላቸው የሚደረገውን ውድድር ከፍ የሚያደርግና ለደንበኞች የሚሰጡትን የጠቀሜታ ሁኔታዎች ለማሻሻል ይረዳል።

*ይህ መመሪያ በሚከተሉት ርዕሶች ሥር ያሉትን መረጃዎች ያጠቃልላል፤*

- በተለየ ሁኔታ ለማወቅና ለማነጻጸር (ለማወዳደር) የትኛው ይጠቅማል?
- በባንክ ሒሳቤ የማድርጋቸውን ድርጊቶች እንዴት አድርጌ መመርመር እችላለሁ?
- ቀጥታ በሆነ ሁኔታ ሒሳባቸውን መመርመር ለማይችሉ ደንበኞች መደረግ ያለበተን ሁኔታ
- በተንቀሳቃሽ የባንክ ሒሳብ (ኦቬር ሸሻቭ) አማካኝነት የሚፈጸም ተመራጭነት ያለው ምርመራ፤
- የዱቤ መገባያ ካርዶችን (ካርቲስ አሽራይ) በተመለከተ ተመራጭነት ስላላው መመርመሪያ ስልት፤
- ማሽካንታ (የቤት መግዣ ብድር) በሚወሰድበት ጊዜ ተመራጭነት ስላለው መመርመሪያና ስልት፤

- የአገልግሎትና የክፍያ ማሻሻያው ደንብ ከፍ ያለ ውጤት ሊያስገኝ እንዲያስችል የሚያደርግ ተመራጭነት ስላለው የድርጊት (የአፈጻጸም) ቅደም ተከተል፤

<u>በተለየ ሁኔታ ለማወቅና ለማነጻጸር (ለማወዳደር) የትኛው ይጠቅማል?</u>

ሁሉም ደንበኛ ተንቀሳቃሽ የባንክ ሒሳብ (ኦቬር ሸሻሽ) ቁጥጥሩን (በተለይ ባንኮቹ ለሚሰጡት አገልግሎት የሚወስኑትን ዋጋ፣ የዱቤ መገባያ ካርድ ባለቤት ለመሆን የሚጠይቁትን ዋጋ፣ በዱቤ ካርድ ስንጠቀም የሚከፈለውን ዋጋ (በተለይ ወለድ) እና ሌሎችንም አነጻጽሮ ማወቁ ጠቃሚ ነው። አስታውስ !! የክፍያ ማሻሻያ ደንቡ (ሪፎርማ) በባንኮች መካከል የማነጻጸር ሁኔታው ይቀጥል ዘንድ ሦስት ዋና ዋና ለውጦችን ያመጣል፤

- ተጠቃሚው (ገበያተኛው) ደንበኛው የሚከፍለውን የተወሰኑ የአገልግሎት ክፍያዎች አንድ ላይ አዋህዶ በማሰብና በመጠቅለል ወደ ሚሶ (አንድ ሦስተኛ) ያህል ክፍያው ይቀንሰቸዋል።
- ተመሳሳይ የሆኑት አገልግሎቶች ከአሁን ጀምሮ በሁሉም ባንክ በአንድ ዓይነት ስም ይጠራሉ።
- የተለመዱት የአገልግሎት ክፍያዎች (ተንቀሳቃሽ የባንክ ሒሳብ /አ"ሽ/፣ ማሸካንታዎችናየዱቤ ካርዶች) ምርመራውንና ንጽጽሩን ቀላል ለማድረግ በተወሰኑ ተመኖች (የተወሰነ ወይም የተቆረጠ ዋጋ) አንድ ላይ ይሆናሉ።

<u>በባንክ ሒሳቤ የማድርጋቸውን ድርጊቶች እንዴት አድርጌ መመርመር እችላለሁ?</u>

ደንበኞች የሚያከናውኗቸው ድርጊቶች (በተለይ በተንቀሳቃሽ ባንክ ሒሳባቸው) የመጨረሻዎቹን ውስን ወሮች በወጪና ገቢ ማረጋገጫ ወረቀት አማካኝነት ለመመርመር ይችላሉ። ደንበኛው ለቀደሞቹ ጊዜዎች ባሉት የወጪና ገቢ ወረቀቶች (በፖስታ ቤት በኩል ቢላኩም እንኳን) ባንኮች ለደንበኞቹ መገልገያ እንዲሆኑ ባቀረባቸው የኢንተርኔትና አውቶማቲክ የቀጥታ መገልገያ መሳሪያዎች አማካኝነት መመርመር ይቻላል።

<u>ቀጥታ በሆነ ሁኔታ ሒሳባቸውን መመርመር ለማይችሉ ደንበኞች፤</u>

በሪፎርማው መሠረት፣ በቀጥታ የባንክ መጠቀሚያዎች መጠቀም ለማይችሉ እና በእጃቸው ባለመኖራቸው ምክንያት በካርዶች መጠቀም ለማይችሉ ደንበኞች፣ 4 ጊዜ በወር በቀጥታ ተጠቃሚ የሆኑት ደንበኞች በሚከፍሉት ክፍያ ዓይነት በባንክ ሠራተኞች አማካኝነት አገልግሎት የመቀበል መብት አላቸው። በካርዶች

አማካኝነት ቀጥታ ተጠቃሚ መሆን ካልፈለጋችሁ ካርዶቹን ለባንኩ በመመለስ በወር 4 ጊዜ በባንክ ሠራተኛው አማካኝነት አገልግሎት መቀበል ትችላላችሁ።

**በተንቀሳቃሽ የባንክ ሒሳብ (ኦቬር ሸሻቭ) አማካኝነት የሚፈጸም ተመራጭነት ያለው ምርመራ፤**

በተንቀሳቃሽ የባንክ ሒሳባችሁ በእየለቱ በምታደርጓቸው ወጪና ገቢ ዝርዝሮች (ኦቬር ሸሻቭ) ማወቂያ በሆኑ አገልግሎቶች ላይ ልዩ በሆነ ሁኔታ ልብ የምትሏቸው ነጥቦች፤

* **በእየለቱ የሚፈጸሙ ተደጋጋሚ ድርጊቶች (ፕዑሎት ሾትፎት)** - እነዚህ በቀጥታ በባንክ ሠራተኛው አማካኝነት የምትቀበሏቸው ቀጥተኛ አገልግሎቶች ናቸው።
* **በወር ለምንገለገልበት የገንዘብ መጠን መቆጣጠሪያ (ዓሉት ሚስጌሬት አሽራይ)** - ወለዱን ወይም ወርሃዊ የገንዘብ መጠን መቆጣጠሪያ ክፍያውን
* **የዱቤ መቀበያ ካርዱን ዋጋ (ዓሉት ካርቲስ አሽራይ)** - ለካርዱ አገልግሎት የሚከፈለውን ክፍያ ወይም ዋጋ።
  የእነዚህን ዓይነት ክፍያዎች ዋጋ በባንክ እስራኤል ድረ-ገጽ (አታር ኢንተርኔት) አማካኝነት ለማነነጻጸር ይቻላል። www.bankisrael.gov.il

**የዱቤ ካርዶችን (ካርቲስ አሽራይ) በተመለከተ ተመራጭነት ስላላው መመርመሪያ ስልት፤**

ከዱቤ መውሰጃ ካርዳችሁ ጋር የተያያዙ ነገሮችን አስመልክቶ ልዩ በሆነ ሁኔታ ልብ የምትሏቸው ነጥቦች፤

- **የካርዱ አገልግሎት ክፍያ** - ባንክ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከፈለው ክፍያ በሪፎርማው መሠረት በወር አንድ ጊዜ ብቻ ለካርዱ መገልገያ ይከፈላል። የዱቤ መውሰጃ ካርዶች ባንክ ሲሰጥ የሚጠይቀውን የአገልግሎት ዋጋና የካርቲስ አሽራይ ከኩባንያዎች በቀጥታ ካርዱን ሲሰጡ የሚጠይቁትን ክፍያ ዋጋ ማነጻጸር ጠቃሚ ነው። ደንበኛው ባንኩ የሚሰጠውን ካርቲስ አሽራይ ወስዶ የመጠቀም ግዴታ የለበትም፣ ከፈለገው የካርቲስ አሽራይ በቀጥታ ከኩባንያዎች መውሰድ ይችላል። የአገልግሎት  አሰጣጥ ክፍያ ዋጋ የሚደረገውን ቅናሽ እና በየትኞቹ መመዘኛዎች (ክራይተሪያዎች) ይሰጣል የሚሉትን መመርመር ያስፈልጋል።
- **ረዘም ባለ ክፍያ ለሚሰጡ አገልግሎቶች ዋጋ** - ለብዙዎቹ ደንበኞች በረጅም ክፍያ የመግዛት ድርጊቶችን መፈጸም እንዲችሉ ይደረጋል።

**ማሽካንታ (የቤት መግዣ ብድር) በሚወሰድበት ጊዜ ተመራጭነት ስላለው መመርመሪያ ስልት፤**

ማሽካንታ በምትወስዱበት ጊዜ የወለዱን መጠን በተመለከተ በተለየ ሁኔታ ልብ ማለት ያለባችሁ - የተለያዩ ባንኮች እንሰጣችኋለን የሚሉትን የወለድ መጠን አነጻጽሮ ማወቅ በጣም ተቃሚ ነው።

**<u>የክፍያ ማሻሻያ ደንብ ከፍ ያለ ውጤት ሊያስገኝ እንዲያስችል የሚያደርግ ተመራጭነት ስላለው የድርጊት (የአፈጻጸም) ቅደም ተከተል፤</u>**

1. ወደ ደንበኛው በሚላኩት የወጪና ገቢ ዝርዝር መግለጫ ወረቀቶችና ተደጋግመው የተፈጸሙትን የድርጊት ዓይነቶች በመለየት፣ እንዲሁም ለድርጊቶቹ አፈጻጸም የተከፈለውን ዋጋ በመመርመር የትኞቹ ድርጊቶች በበለጠ ተደጋግመው እንደተፈጸሙ ማወቅ አስፈላጊ ነው።
   ባለው የማነጻጸሪያ ቅጽ መታገዝ ይቻላል፤ **ቅጹን ለማግኘት፡**
   www.bankisrael.gov.il

2. ከባንኩ ጋር ድርድድር በማድረግ በጣም ጥሩ የሆኑ ሁኔታዎችን ለመቀበል መጠየቅ።

3. እነዚህን ለመሰሉ የድርጊት አፈጻጸሞች የሚከፈለውን ዋጋ ከሌሎች ባንኮች አንጻር በማገናዘብ፣ በጣም በተሻለ ሁኔታ ጠቀሜታ ወደሚሰጡ ባንኮች ለመዘዋወር ጥሩ አድረጎ መመርመር። ይህን የመሰለውን ንጽጽር በምታደርጉበት ወቅት ሒሳብ ውስጥ ማስገባት ያለባችሁ፣ ለወርሃዊ የገንዘብ መጠን መቆጣጠሪያ ክፍያውና ለተንቀሳቃሽ የባንክ ሒሳባችሁ ወጪና ገቢ ዝርዝር ወረቀቶች ባንኩ የሚወስደውን ወለድ ነው።

4. ደንበኛው በባንክ ስላሉት አጠቃላይ አጠቃቀሞችና ግዴታዎች የመረጃ ወረቀቶችን መቀበል ይችላል፤ የሚቀበለውም በዓመት ሁለት ጊዜ ያለ ምንም ክፍያ ነው። ይህም ደንበኛው ከአንዱ ባንክ ወደ ሌላው ባንክ ለመዘዋወር የሚያስችለውን ምርመራ እንዲያደርግ ያደርገዋል።

**ባንክ እስራኤል**

## 10 ስለአገልግሎት ክፍያዎች የቁጠባ ዘዴ ምክር (አስተያት)

1. **የቁጠባ ሒሳባችሁን ሁኔታ መርምሩት! ከባንካችሁ ሒባታችሁንና የምትከፍሉትን ዕዳዎች ዝርዝር መቀበል ትችላላችሁ፡፤**
ሒሳባችሁን ወደ ሌላ ባንክ ለማዛወር በምትፈልጉበትም ጊዜ፣በዓመት ሁለት ጊዜ ያለ ክፍያ ዝርዝር መግለጫዎችን መቀበል ትችላላችሁ፡፤

2. **ሒሳባችሁን ከመያስተዳደረው ባንክና ከሌላው ባንክ መካከል ያለውን የክፍያና አሠራር ሁኔታ አጥኑት፡፡**

- ከናንተ ሁኔታ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ክፍሎች በማጥናት፣ባንካችሁ ልዩ ልዩ ድጋፎችንና የክፍያ ቅነሳዎቸን እንዲያደርግላችሁ ጥያቄ ማቅረብ ትችላላችሁ፡፡

- ስለሒሳባችሁ አስተዳደር ሁኔታ ከባንካችሁ ጋር ውይይት ማድረግና፣ ስለ አገልግሎትና ስለ ወለድ ክፍዎች ጉዳይ ቀናሽ የምታገኙበትን መንገድ እንዲያስገኝላችሁ መጠየቅና ማስፈጸም ትችላላችሁ፡፡

- ወደ ሌላ ባንክ ለመዛወር ሁኔታዎችን መርምሩ **አስታውሱ ! ወደ ሌላ ባንክ ስትዛወሩ የምትከፍሉት ክፍያ መጠን ዛሬ በጣም ቀንሷል፡፡** ( እስከ 40 ሽ/ል ለሒሳባችሁ አና ለዱቤ ካርዳችሁ( ካርቲስአሽራይ) 40 ሽ/ል ተጨማሪ ትከፍላላችሁ ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ሌላ ሶስተኛ አካል ካለም እንዲሁ፡፡

3. **የቁጠበ ሒሳባችሁን በቀጥተኛ የሒሳብ አያያዝ ዘዴ አሠራር ተጠቀሙ !** የምትከፍሉት የአገልግሎት ዋጋም ለቋሚ ክፍያዎች፣ ለቸክ፣ ለሒሳብ መከታያ ወረቀቶቸ የሁሉም አገልግሎት ዋጋ አንድነት ሲሆን ይቀላል ማለት ነው፡፡ በኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች ተጠቀሙ፣ ለምሳሌ በኢንተርኔት፣ በተሌፎንና በማክሸብ መጠቀም ክፍያዎችን ይቀንሳል፡፡

**አሰታወሱ! ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ማለት እንደ ገንዘብ ማሰገባት፣ ገንዘብ ማውጣት፣ ብድር መውሰደድ፣ በጨረታ ግዥና ሽያጭ ላሉት አገልግሎቶች በክፍያ አትገደዱም ፡፡ ከባንክ ሠራተኞች ድረስ ቀርባችሁ አገልግሎት ብትቀበሉም የአገልግሎት ዋጋ አይከፈልብትም፡፡**

4. **በቀጥታ የምትገለገሉባቸው መሳሪያዎች ማለት እንደ** መረጃ ማውጫ ካርድ፣ የዱቤ መግዣ (ካርድካርቲስ አሽራይ) ፣ ገንዘብ መምዘዣ **ካርድ፣ካሏችሁና የማትጠቀሙባቸው ከሆነ፣ በቀጥታ ወደ ባንካችሁ መልሳችሁ፤ ከባንክ አገልግሎ ክፍያ ነፃ መሆን ትችላላችሁ፡፡**

5. ያላችሁን የዴቢ መግዣ ካርድ አገልገሎት ክፍያ ዋጋ፣ከሌሎች ኩባንያዎች የክፍያ ዋጋ ጋር በማወዳደር ልዩነቱን እወቁ፡፡ **አሰታውሱ!** ከባንካችሁ የዴቢ መግዣ ካርድ (ካርቲስ አሽራይ)፣ አውጣችሁ እንድትይዙ ምንም ግዴታ የለባችሁም፡፡

6. **በዴቤ መግዣ ካርድ ( ካርቲስ አሽራይ )፣ የምትከፍሉትን ዕዳዎች በአንድነት ሰባሰባችሁ መርምሩት!** የወሩ ዕዳችሁ ተሰባስቦ አንድ የአገልግሎት ክፍያ ብቻ በመክፈል መጠኑን ትቀነሳላችሁ ማለት ነው፡፡በዚህ ዓይነት ካደራጃችሁ የአገልግሎት ዋጋ ክፍያችሁን ትቆጥባላችሁ፡፡

7. **የዴቤ መግዣ ካርድ ( ካርቲስ አሽራይ ) አጠቃቀማችሁን ተከታተሉ፣** በሁለት **የዴቤ መግዣ ካርድ ( ካርቲስ አሽራይ )**፣ እንዲያውም የምትጠቀሙ ከሆነ ደግሞ ክፍያችሁ የበለጠ ይቀንሳል፡፡ **አስታውሱ!** የሚገባችሁ የአገልግሎት ክፍያ ቅናሽ **በዴቤ መግዣ ካርድ ( ካርቲስ አሽራይ )**፣በምትጠቀሙበት መጠን ይወሰናል፡፡

8. ከአንድ በላይ **በዴቤ መግዣ ካርድ ( ካርቲስ አሽራይ)** የምትጠቀሙ ከሆነ አስፈላጊነቱን መርምሩት! የማትጠቀሙባቸው ካረዶች ካሉ መልሷቸው፡፡

9. **የተበታተኑ ክፍያዎችን ከመፈጸም ተወገዱ!** ከፊል የባንክ አገልግሎት ክፍያዎች አነስተኞች ናቸው፡፡

10. **የተበታተኑ ክፍያዎችን ስለ መፈጸም ያላችሁን ሁኔታ አስፈላጊነቱን መርምሩ!** ብዙ ክፍያዎችን ቆራርጣችሁ በካርድ ከከፈላችሁ ኩባንያዎች ለእያንዳንዱ ክፍያ ስለሚጠይቁ ብዙ የአገልግሎት ክፍያ ይጠይቋችኋል፡፡ በጥቃቅን ገበያዎች በካርድ ከመተቀም ተወገዱ፡፡

**ተጨማሪ ምክሮች፡**

**ማወዳደር ስታደርጉ ከዚህ የሚከተለውን አስተውሉት፡**

- **የተሸሻለውን ክፍያ ተመን**
- **የቁጠባ ሒሳባችሁን ማስተዳደሪያ ቅጽ**

  **አድራሻ :** www.bankisrael.gov.il

- **መረጃዎችን ማወዳደር፡ በባንኮች የቁጥጥር አካል በይፋ ይገለጣል፡፡**

  **አድራሻ፡** www.bankisrael.gov.il

**ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች መልሶች ተመልከት፣**

ለልዩ ደንበኞች ዓይነት ቡድን የሚደረገው ቅናሽ ወይም ጥቅማ ጥቅም ይደርሳችኋልን;

**የወለድ መጠን ምን እንደሆነ መርምሩ፡**

- **በገንዘብ ቁጠባ ገቢዎች፣ - አስታውሱ!** ቁጠባ ሒሳባችሁን በሌላ ባንክም ማስገባት ትችላላችሁ ( ከባንካችሁ ውስጥ ብቻ ግድ መሆን የለበትም) በአዲሱ የተሻሻለው ድንብ መሰረት የባንክ ሒሳብ ለማስተላለፍ የሚከፈለው ክፍያ ተቀንሷል፡፡ይህም በአንድ ክፍያ ብቻ እንዲወሰን ተደርጓል፡፡ **ከሌሎች ባንኮች ያለውን የወለድ መጠን አወዳድሩ !!**
- **በዱቤ ግብይት ጣራ አጠቃቀም - በዚህ ጉዳይ / አገልግሎት ይከፈል የነበረው የባንክ የአገልግሎት ዋጋ ተሰርዟል። የቀረው የወደልዶችን መጠን ማወዳደር ብቻ ነው።**
- **በብድሮች ጉዳይ - እስከ 50000 ሽ/ል ድረስ ልሚወስዱ ብድሮች ይከፈል የነበረው የባንክ የአገልግሎት ዋጋ ተሰርዟል። የቀረው የወልዶችን መጠን ማወዳደር ብቻ ነው።**

# ባንክ እስራኤል

## ስለ ባንኮች ቁጥጥር

### ስለ ባንክ አገልግሎት ክፍያዎች ጉዳይ የወጣ አዲስ የማሻሻያ ደንብ

### ጥያቄዎችና መልሶች

ከ-1.7.2008 ጀምሮ ስለ ባንክ አገልግሎች ክፍያዎች የወጣው የማሻሻያ ደንብ በሥራ ላይ የሚውል ሲሆን፣ ተግባሩም አሁን ያሉትን ባንኮች ከደንበኞቻቸው ሒሳብ ላይ ለአገልገሎትየሚወስዱትን ክፍያዎች በብዛት ይቀንሳል ተብሎ ይታመናል፡፡

**1. ስለ ባንክ አገልግሎት ክፍያዎች የውጣው አዲስ ደንብ ምንድን ነው?**

በአዲሱ ደንብ መስረት ስለ ባንክ አገልግሎት አንድ ወጥ ይሆን ዝርዝር ተመን እንዲወሰን የቁጥጥሩ ክፍል ደንግጓል። ባንኮቸ በዚህ ዝርዝር መሠረት ደንበኞችን የማስከፈል መብት ይኖራቸዋል። ቁጥሩ ብዙ ዓይነት የነበረው የክፍያ ዝርዝር ጥናትና ምርምር በጥሩ ሁኔታ ከተዲደረገበት በኋላ፣ ባንኮች ማስከፈል ያለባቸው ክፍያ አጠርና ግለጽ በሆን አዲስ ዝርዝር እንዲደራጅ ደንቡ ያስገድዳል።

**2. የውጣው አዲስ ደንብ መሠረቱ ምንድን ነው?**

ባንኮች ለአገልግሎታቸው የሚጠየቁትን ክፍያ ሁኔታ በተመለከተ አዲስ ምርመራ እንዲደርግ በ2007 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ የተቋቋመው ከፍተኛ የቁጥር ኮሚቴ ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ የደንብ ሐሳብ አቀረቧል። ይህን ሐሳብ መሠረት በማድረግ፣ ከደንበኞች ስለሚጠየቀው የአገልግት ክፍያ አዲስ ደንብ ተደነገ፣ (የማሰተካከያ ወይም የእርማት ቁጥር 12 2007 ዓ.ም.)።የባንክ አገልግሎቶች ዓይነትና የክፍያዎች መጠን ተወሰነ። አዲስ የወጣው የክፍያ ማስተካከያ በሶስት ዋና ዓይነቶች ተምድቧል፡ ይኸውም የሒሳብ መቀበያና ማስተላለፊያ መደበኛ እንቅስቃሴ (ወጪ ገቢ ሒሳብ)፣ "የሚሽካንታዎችና" የዱቤ መገባያ / የክሬዲት( ካርቲሰ አሽራይ )፣ የዱቤ መገባያ ካርዶች አገልግሎት ክፍያዎች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ባንኮች ለደንበኞቻቸው ማሳወቅ ሰላለባቸው አገልግሎቶችና ክፍያዎች ጉዳይ ተጠንቷል። እንዲሁም በተጨማሪ ባንኮች ለደንበኞቻቸው ማሳወቅ ሰላለባቸው አገልገግሎቶችና ክፍያዎች ጉዳይ ተበራርቷል።

**3. የእሰራኤል ብሔራዊ ባንክ በአዲሱ ደንብ ስለ ባንኮች ቁጥጥር ያለው ሥልጣን ምንድን ነው?**

በደንቡ ከየተስጠው ሥልጣን የባንኮች ድርጅት ለአገልግሎት የሚጠይቀውን ክፍያዎች አንድ ወጥ በሆነ የማሰከፈያ ዝርዝርና የክፍያውን መጠን ግልጽ በማድረግ ማዘጋጀትና ማቅረብ እንዳለበት ማስፈጽም ነው።

ባንኮችን ላይ የሚገረገው የጥጥር መብት የሚያተኩረው በክፍያ ዓይንቶችና መጠናቸው ተገቢ የሆነ ቅናሽ እንዲደረግበት ነው። ለእሰራኤል ብሔራዊ ባንክ የተስጠው ተጨማሪ መብት፣ የባንኮችን የክፍያ መጠን በማወዳደር ለደንበኞች ማሳወቅና በዚህ መልኩ ውድድር እንዲፈጠር ማድረግ ነው።

**4. ደንቡ ከመቼ ጀምሮ ሥራ ላይ ይውላል?**

**ከ 1.7.2008.ዓ.ም. ጀምሮ ደንቡ ሥራ ላይ ይውላል።**

**5. የአዲሱ ደንብ ዋና ዓላማ ምንድን ነው?**

የአዲሱ ደንብ ዓላማ ባንኮች የሚያስከፍሉትን የአገልግሎት መጠን ለሕዝብ በግልጽ እንዲያሳውቁና ውድድር እንዲጠናከር ማድረግ ነው።ይኸውም የባንኮች ደንበኞች የሚከፍሉትን መጠን በትክክል አውቀው የራሳችውን የተሻለ ውድድርና አማራጭ ለማደረግ እንዲረዳቸው ነው። በዚህም ዘዴ ወደ ሌላ አማራጭ የተሻለ ባንክ ለመዛወር ይረዳቸዋል። ይህ ውድድር ባንኮች የሚሰጡትን አገልግሎጥ እንዲያሻሽሉም ያግዛቸዋል።

**7. በአዲሱ ደንብ መውጣት የሚደረጉት ዋና ለወጦች ምንድን ናቸው?**

አዲሱ ደንብ አራት ለውጦችን ያመጣል፤

- የአገልግሎት ክፍያዎች መጠን በሲሶ እጅ ( በአንድ ሶስተኛ እጅ ) ደረጃ ይቀነሳል፡ ይህም ክፍያዎችን በማዋህድ ጭምር የሚፈጸም ይሆናል።
- ተመሳሳይነት ያላቸው የባንክ ክፍያዎች በሁሉም ባንኮች ዘንድ በአንድ ስም እንዲጠሩ እንዲታወቁ ይሆናል።
- የክፍያዎች መጠን በሁሉም ባንኮች አሠራር አንድ ዓይነት ይሆናል።ዋና ዋና ክፍያዎች ለምሳሌ ሚሽካንታዎች፣ የዱቤ መገባያ ካርዶች አገልግሎቶች በአማካኝነት በተዋሀደ ዘዴ የደራጃሉ። የክፍያው መጠንም ለደንበኞች የማወዳደር ፍላጎት እንዲያመች ሆኖ ይቀርባል፡

**8. በወጭና ገቢ ሒሳቦች ላይ ምን ለውጥ ይደርጋል?**

በአዲስ ከተሻሻለው ደንብ በፊት ለወጭና ገቢ ሒሳብ 15 የአገልግሎት አይንቶችና ክፍያዎች የነበሩ ሲሆን፣ አሁን ግን 2 አይነት ብቻ እንዲሆን ተደርጓል። ይህም ቀጥተኛ ለሆኑ ተመሳሳይ አገልግሎቶች ( በሒሳቡ ባለቤት በቀጥታ የአሠራር ዘዴዎች ( በአ"ሽ - የቁጠባ ሒሳባችን ) ከንውኖች በጠታ ሊመክታትል እንዲችሉ በማድረግ ነው። የባንክ ደንበኞች በኢንተርኔትና በኮምፒተር በሚታገዝ ቴክኖሎጅ በመጠቀም ብዙውን የአግልግሎት ወጭ (አምላ) ሊቀንሱት ይችላሉ ማለት ነው።

**በትክክል ልብ በሉ !** ገንዘብን ገቢና ወጭ በማድረግ ፣ ብድር በመውስድና በመመለስ፣ እንዲሁም ዋሰትና ባላቸው ስነዳዊ የንግድ አሠራሮች (ንያሮት ኤሬህ ) የሒሳብ

እንቅሳቃሴዎች፣ የአገልግሎት ክፍያ ግዴታ የለባችሁም፡ አገልግሎቱን የባንኩ ሠራተኞች ቢሠሩትም ክፍያ አይጠየቅበትም።
ከአዲሱ ደንብ በኋላ በቁጠባ ሒሳብ ላይ የሚታየው የአገልግሎተ ክፍያዎች 2 ብቻ ናቸው። ደንበኞች በቀጥታ የሚፈጽሙት የባንክ አገልግሎትና የባንኩ ሠራተኞችም ቢሆኑ ለሚሰጡት አገልግሎት  2 ክፍያዎች ብቻ ይወስናል።

## 9.  ሒሳባቸውን በቀጥታ አሠራር ለማንቀሳቀስ ችሎታው የሌላቸው ደንበንኞች ምን ማድረግ ይችላሉ?

በማሻሻው ደንብ መሠረት፣ሒሳባቸውን በቀጥታ አሠራር ለማንቀሳቀስ ችሎታው ለሌቸው ደንበኞች፣ በዚህ ዘዴ ለመገልገል ካረቲሱ ለሌላቸው ሁሉ፣ በባንኩ ሠራተኞች አማካይነት በመገልገል በወር 4 እንቅንቃሴዎች ማድረግ የሚችሉ ሲሆን፣ ክፍያው ከቀጥታው አሠራር ክፍያ ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል።

## 10.  በዱቤ መገባያ ካርድ ሁኔታ (ክሬዲት) አሠራር ዋናዎቹ ለውጦች ምን ምን ናችው?

ከተሻሻለው ደንብ በፊት በዱቤ ሒሳብ አሠራረርና አያያዝ ላይ ከወለዶች በተጨማሪ የአገለግሎት ክፍያዎች ነበሩበት፣ አሁን ግን በዚህ ለዱቤና ለብድር ስንድ አሠራርና አያያዝ አገልግሎት ልዩ ክፍያ አይደርግበትም፤ የአግልግልት ክፍያው ተስርዟል። ክፍያ የሚጠየቀው የዱቤ አሠራር ማለት በወር በዱቤ ለምንጠቀምበት የገንዘብ መጠን መቆጣተሪያ "ሚስጌሬት አሽራይ" ለሌላቸው ብቻ ይሆናል ማለት ነው።

## 11. ሰለ ብድር ጉዳይ ያሉት ለውጦች ምንድን ናቸው?

ከአዲሱ ደንብ መውጣት በፊት የተውሰኑ ( ከብድር ወለድ ተጨማሪ) ሁለት ክፍያዎች ( አምሎት) ነበሩ - የዱቤ ሒሳብ ገደብና የብድር መክፈያ ሠንዶች አገልግሎት ክፍያዎች ናቸው። በአዲሱ ደንብ መሠረት ግን እነዚህ ክፍያዎች ማልት እስከ 50000 ሽ/ል ድረስ ( ሰለ ቤት ግዥ ካልሆነ በስተቀር) ፤ እንዲሰረዙ ተደርጓል።

## 12. በዱቤ መገባያ ሒሳብ ( ካርቲስ አሽራይ) አሠራር ላይ ምን ልውጥ ተደርጓል?

ከአዲሱ ደንብ መውጣት በፊት በዱቤ ሒሳብ (ካርቲስ አሽራይ) አሠራር በ-3 ክፍያዎች የተከፈለ ነበር - ወርሃዊ የሒሳብ እንቅስቃሴ አስተዳደር፣ ( ወርሃዊ ክፍያ)፣ ሃላፊነትን የመገደቢያ ክፍያ፣ ( አመታዊ ክፍያ) ( ዓመታዊ ).
ከአዲሱ ደንብ ግን የዱቤ ሒሳቦች አሠራር ( ካርቲሴ አሽራይ) በአንድነት " በውርሃዊ ክፍያ ብቻ " ተጠቃሎ እንዲከፈል ተደርጓል፡፡

በውርሃዊ የካርቲሴ አሽራይ ክፍያዎች በየወሩ እንዲከፈል፣ ይኸውም በሚወሰነው መመሪያ ( ከሪተሪዎን - መመዘኛ መሠረት) ኩባንያዎች ለደንበኞቻቸው የሚያደርጉት ቅናሽና ሌላም ጥቅሞች በየውሩ እንዲሰጧቸው ለማስቻል ነው፡፡

## 13. በአድሱ ደንብ መሠረት የአገልግሎት ክፍያዎች ይቀነሳሉን?

ዓላማው  የተለያዩ ክፍያዎችን መቀነስ ሲሆን፣ በራሱም ፣ የባንክ አገልግሎቶችን ማስረክሰ ሳይሆን፣እዲያውም፣ ባንኮች ገቢያቸው የሚቀንስባቸው መኑን ከወዲሁ ቢያውቁትም፣ ደንበኞች

ግን የተሻለ ቁጠባ ሊያገኙ እንዲችሉ ነው ። በተጨማሪም፣ ለሩቅ ጊዜ፣ የደንበኞች እውቀትና ንቃት እየተጠናከረ ሲምጣ፣ ባንኮች የሚጠይቁን ክፍያዎች በመገንዘብ ድርድር ለማድረግ ስለሚያስችላቸው ፣ የልዩ ልዩ አገልግሎቶችን አስፍላጊነት ተከታትለው አላስፈላጊ ወጭዎችን እንዲቀንሱ ያስችላቸዋል።

14. **አዲሱ ደንብ ለየትኞቹ ደንበኞች ነው የውጣው ?**

**አዲሱ ደንብ ለሁሉም የባንክ ደንበኞችን " የግል ደንበኛ " ለድርጅቶች " ትናንሽ የግል ንግድ ሥራ ድርጅቶች " ነው።**

**የግል ደንበኞች፣**

እያንዳንዱ ደንበኛ ማለት የግል ደንበኛ ሲሆን፣ እሱም ከአነስተኛ ድርጅት " ከግል ባልፈቃድ ሠራተኛ " ጋር ይለያል።

**አነስተኛ የግል የሥራና ንግድ ድርጅት**:

1. **አነስተኛ ድርጅት ማለት የጋራ የሥራ ቤት ተወካይ ነው**1.
2. ገና ዓምት ያልሞላው ድርጅት ነው
3. ድርጅት፣ ለባንክ ዓምታዊ ሪፖርት ያቀረበ፣ ካለፈው ሪፖርቱ ጀምሮ **ከአንድ ሚሊዎን ሽ/ል** በላይ ያልሀነ

 በሕጋዊነት የተቋቋመ ድርጅት፣ በድርጅቱ አባላት የሆኑት ድንበኞች ሁሉ ሌላ የግል ሥራ የሌላቸው ካልሆኑ በስተቀር።

15. **የአገልግሎት ክፍያ ተመን የቱ ነው?**
 መደበኛ ተመን ማለት ወጥ በሆነ ዝርዝር ሰነድ መስረት የተጠቃለለ የአገልግሎት ክፍያ፣ ለባንኮች በተስጠው መብት መሰረት የተመደበና የተደራጀ ማለት ነው። በባንኮች አጠቃላይ መመሪያ መሰረት (ለደንበኞች አገልግሎት ክፍያ) 2008 ዓ.ም. መድብኛ ተመን

 **"ለ"ግለሰብ" ደንበኛና ለአነስተኛ የግል ሥራ ድርጅት** ማለት የአመት ካፒታሉ እስከ አንድ ሚሊዎን ሽ/ል የሆነ ሲሆን፣ ባንኮች የመጀምሪያውን የአገልግሎት ክፍያ ተመን ለደንበኞቻቸው በቀጥታ ወይም በኢንተርኔት ማሳወቅ አለባቸው።

16. **የተሻሻሉት የክፍያ ተመኖች ደንበኞች እንዲያውቋቸው በባንክ ተዘጋጅተው መገኘት አለባቸው።**
 ይኸውም በባንኩ ድራ ገጽ ( የኢንተርኔት ፋይልስ ) ወይም በሌላ መንገድ መረጃው መተላልፍ አለበት። ደንበኞች ለአገልግሎት ወደ ባንክ ሲቀርቡ የክፍያዎች ሰነድ እንዲሰጣቸው መድረግ አለበት።

17. **በቁጥጥር ላይ ያሉ የክፍያ አይንቶች**

ከዚህ በታች የተጠቀሱት ክፍያዎች አዲሱ ደንብ ከወጣም በኋላ በቁጥጥር ስር ያሉ ክፍያዎች ናቸው።

| የክፍያው ስም | የክፍያው መጠንና / አስተያየት |
|---|---|
| የተለመደው የቸክ ጥራዝ ዋጋ | ለታወቀውና በስፋት ለሚገኘው ቸክ ማለት ሲሆን ፣ በጥራዙ ካለው ለያንዳንዱ ቸክ 36 አጉሮት ክፍያ ተውስኗል |
| የመርጃ ካርቲስ | ሰለ ሂሳብ መረጃ መቀበል፣ ደንበኛው ከባንክ ሲቀበል፣ በካርቲሱ ተጠቅሞ መረጃ ሲያወጣ ለአመት 8 ሽ/ል ይከፍላል |
| የቁጠባ ሒሳብን ለማስተዳደር፣ ለመኖሪያ ቤት ግኘ ብድር | የመኖሪያ ቤት ሲገዛ ባንኩ ለሚያካሂደው አገልግሎት የሚከፈል ዋጋ ነው፡ የብድሩ ገንዘበ በየወሩ በተከፈለ ቁጥር የሚወስድ የባንክ አገልግሎት ክፍያ ነው። የክፍያው መጠን 2 ሽ/ል<br>እንዲሆን ተወስኗል፡ በየወርሩም ይከፈላል |
| የቤት መግዣ ብድር ሰምምነት | ይህ ሰለተወሰደ የቤት ብድር ሒሳብ አያያዝ ጉዳይ ነው |
| በሌላ ባንክ ( አብዛኛውን በቤት መግዣ ) ተመሳሳይ ደረጃ | ንብረቱ ወደ ሌላ ባንክ እንዲመዘገብ ስምምነት በተደረገው መሰረት፣ ማዛወሩ አስፈላጊንት ሲኖረው፣ በአጠቃላይ ደንበኛው ሌላ ተጨማሪ የባንክ ብድር ሲፈልግና፣ንብረቱ በመያዣነት ሲመዘገብ፣ ወይም የወሰደውን ብድር አጠቃሎ ወደ ሌላ ባንክ ማዛወር ሲፈልግ 150 ሽ/ል ክፍያ ይጠየቃል |
| ባንኩ የደንበኛውን "ናያሮት ኤሬሀ" ወደ ሌላ ባንክ ቢያስተላልፍ ( አብዛኛውን ጊዜ ከሌላ አጋር ጋር / ከምስቱ ጋር  ቢሆን... | ይህም አንድ ደንበኛና ናያሮት ኤሬሁን ወደ ሌላ ባንክ ማዛወር ሲፈልግ ነው። ይህ ሁኔታ ደንበኛው ናያሮት ኤሬሁን እሱ አንድ ሽርክ በሆነበት ኩባንያ ሊያዛውር ሲፈልግ የሚፈጸም ጉዳይ ነው።ለዚህ የሚከፈለው መጠን 5 ሽ/ል ይሆናል ። ከዚህ ተጨማሪ አስተናጋጁ ባንክ ይህን ለማስተናገድ ለሌላ ባንክ የከፈለውን ወጭ ተመላሽ ለማድረግ የሚከፈል ነው። |
| የውጭ ገንዘብን ምንዛሬን በአገር ውስጥ ለደንበኞች ሒሳብ ማስተላልፍ | ይክውም የውጭ ምንዛሬን ከደንበኛው ሒሳብ ወደ ሌላው የባንክ ሒሳብ በሚተላልፍበት ጊዜ ነው። |